# ይነግር በይፋ

ለተሻለች ኢትዮጵያ (By BetterEthiopia  betterEthiopia@yahoo.com )

በአለማችን  የሰለጠኑ አገሮች የምንላቸው ከሚያስገርም ገጽታዎቻቸው መሀል አንዱ ያለማቋረጥ ማሻሻልን ማሳየታቸው ነው። በአንጻሩ ደግሞ ከአለም ያልበለጸጉ አገሮች የሚያሳዝን ገጽታቸው ብዙ መሻሻል አለማሳየታቸው ነው። መሻሻል የዘመናዊ ሁኔታዎች አዎንታ ነው። አዲስ መኪና ለሽያጭ ሲቀርብ ተተኪው አዲስ አይነት መኪና እየተዘጋጀ ነው። አንድ የኮምፒውተር ፕሮግራም እንድሁ ለተጠቃሚዎች ሲከፋፈል የሚቀጥለው ቨርዥን በእቅድ ላይ ነው። የአንድ የሰለጠነ ከተማ ነዋሪ አንዱን የከተማ ክፍል ሳይጎበኘው ጥቂት አመታት ቢያልፉ ተመልሶ በሚሄድበት ሰአት የሚያየው አዲስ ነገር እጅግ በጣም አስገራሚ ነው። ይህ ሁሉ መጠነ ሰፊ ለውጥ እንዴት ተግባራዊ ሆነ? ለለውጥስ ምን  ነገሮች አመቺ ናቸው ብሎ መጠየቁ ካልበለጸጉ አገሮች ለተፈጠርን ሰዎች የግድ ነው። ምክኒያቱም ምንም እንኳን ግለሰቦች የትም ይወለዱ አመቺ ሁኔታ ከተፈጠረላቸው ከሰለጠኑ ሃገሮች  ከተወለዱ ሰዎች ጋር በቀላሉ ተወዳዳሪ መሆን መቻላቸውን በተሳካላቸው የታዳጊ አገሮች ዲያስፖራ ማየት ችለናል። ቁም ነገሩ የግለሰቦች መሻሻል ሳይሆን የመላው የሀገር ሁኔታ መሻሻል  ነው። ስለዚህ ለውጥ እንደሚያስፈልገን(ለዚያውም ፈጣን የሆነ) ሁላችንም የምንስማማበት ጉዳይ ነው። ከሰለጠኑ ሀገሮች የምንናስተውለው  ለውጥን ማምጣት የሚያስመሰግንና የሚያስሸልም ሲሆን ነገር ግን ባልበለጸጉ ሀገራት ለውጥን ማምጣት አስቸጋሪ ነው።

*ምንድን ነው በሰለጠኑ ሀገራት ለውጥን ለማምጣት የሚያደፋፍረው ሁኔታ?*

የዚህ መሰረቱ የአስተሳሰብ እና ሀሳብን የመግለጽ ነጻነት መኖሩ ነው። ከትምህርትም ሆነ ከተሞክሮ ወይም በሌላ አጋጣሚ የታሰሰውን ጠቃሚ ሀሳብ በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አግኝቶ ተግባራዊ ማድረግ፤ የሰለጠኑ አገሮች የሚያደርጉትን የማያቋርጥ የመሻሻል ሂደት የመሰለ ሁኔታ ኋላቀር በሆኑ ሀገራት ላይ እንዲደገም ያስፈልጋል። አሁን ባለው አለማቀፋዊ የሆነ የመገናኛ መረቦች መዘርጋት፣ የኢኮኖሚ ትስስር፣ የባህል እና የትምህርት ልውውጥ የአለም እውቀት በግለሰቦች ጣት ጫፍ እንዲሆን አድርጓል። ማን ምን እንዳወቀ አይታወቅም እንጂ እውቀቱ በአንድ ሀገር ነዋሪዎች ውስጥ አለ ማለት ያስደፍራል። ይህ እውቀት ተግባራዊ ቢሆን ባፋጣኝ ሁኔታ አንድን ሀገር ማሻሻልና ያሉባትን ችግሮች ባስቸኳይ ማስወገድ የሚያስችል የአእምሮ ሀይል አለ። ጥያቄው ይህ የጋን ውስጥ መብራት የሆነ እውቀት ከፍ ብሎ እንዲያበራና የዚህ እውቅት ተሸካሚ የሆኑ ግለሰቦች ተደማጭነት እንዲኖራቸው ምን ቢደረግ ይሻላል የሚለው ይሆናል።

በኢትዮጵያውያን መካከል የበጎ ምኞት አመለካከት ከራስ አንጻር(በራሳችን ዓይን ስለራሳችን ባለን አመለካከት ግምት ውስጥ) በብዛት ይገኛል። ሆኖም ግን ያንዱ የበጎ ፍላጎት ሀሳብ ከሌላው የበጎ ሀሳብ ሀሳቢ ጋር የሚለይ ብሎም የሚጋጭ ሲሆን ይስተዋላል። በበጎ አላማ ስም ወይም በታላቅ የተከበረ ግብ ስም ጥቃቅን የሚመስሉ ጥፋቶችና ግድፈቶች ሲፈጸሙ በቀላሉ ሳይታረሙ እየታለፉ በተግባር ትጋትን የሚቀንሱ መብትን የሚነፍጉ እለታዊ ድርጊቶች ይፈጸማሉ።የሐሳብ ትክክለኛነት ሚዛኑ የሀሳቡ ደጋፊዎች ወይም ተቃዋሚዎች ቁጥር ብዛት አይደለም። አንዳንዴ የሀሳብ ትክክለኛነት ሚዛኑ ጊዜና በተግባር ከዋለ በኋላ የሚደረግ ግምገማ ነው።

በታሪክ እንደታየው አንዳንድ ስር ነቀል የሆነ አስተሳሰብ ያፈለቁ ግለሰቦች በዘመናቸው ሲሰደዱና ሲወገዙ ኖረው በድህረ ዘመናቸው ደግሞ ሲሞገሱ ታይተዋል። ለአብነት ያህል እነጋሊሊዮ ጋሊሊን መጥቀስ ይቻላል። የዚህ ጽሁፍ አላማ ሰዎች የማይስማሙበትን ሀሳብ እንዲቀበሉ ለማደርግ አይደለም። ነገር ግን ከተለመደው የተለዩ ሀሳቦች ለበቂ አድማጮች ሳይገለጹ ገና በእንጭጩ  ሲወገዙ እና የሀሳቡ አፍላቂዎች ተስፋ እንዲቆርጡ በሚያደርግ ሁኔታ ሀሳባቸው ሲገታ ጠቅላላ ማህበረሰቡ የሚጎዳ መሆኑን ለመጠቆም ነው። ማንም ግለሰብ የፈለገውን ያህል የተማረና የተመራመረ የታወቀና የተከበረ ቢሆንም በአለም ለሚፈጠሩ አስተሳሰቦች ትክክለኛነት ወይም ትክክለኛ አለመሆን የፍጹም እውቀት ስልጣን አለኝ ብሎ ሊገምት አይገባውም። አንዳንዴ ተማሪዎች ከአስተማሪዎቻቸው የላቀ ሃሳብ ተሸካሚ ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲሁም እንዳንዴ ልጆች ከወላጆቻቸው የተለየና የተሻለ አስተሳሰብ ሊያራምዱ ይችላሉ። ስለዚህ ማንም ሰው እራሱን እንደ እውቀት መጨረሻ ባለቤት አድርጎ መቁጠር የለበትም። ወይንም የታወቁት አቶ እገሌ ካሉ አውነት ነው ወይም እሳቸው አሌ ካሉ ሀሰት ነው ብሎ  የተናጋሪውን ማንነት በመመርኮዝ አንድን ሃሳብ ትክክል ነው ሊባል አይገባም።

በመሰረቱ አንድን ሀሳብ  ለመቃወምና ለማጣጣል አርቆ አስተዋይነት፣እውቀት፣ ጨዋነትና የሰለጠነ ባህሪ አይጠይቅም። ማጣጣልና ማባጨጭ ልዩ ችሎታ አይጠይቅም። ጸባይ የጎደለው እውቀት ያነሰው ወይም ማሰብ የደከመው ሰው በቀላሉ የሌላውን ሰው ሀሳብ ሊያወድቀው ወይም ዝቅ ሊያደርገው ይችላል። በአንጻሩ ግን የአንድን አስተሳሰብ ጥልቅነትና ጠቃሚነት ለማድነቅ በጎ ህሊና፣ እውቀትን፣ አርቆ አስተዋይነትና አሳቢነትን ይጠይቃል። በአንድ ቀልድ ለመሳቅ ቀልዱ እንዲገባን ያስፈልጋል። ስለዚህ አዳዲስ ሀሳቦች በቁም ነገር፣  አግባብ በሆነ ቦታና ሰአት በሚነሱበት ሁኔታ ሃሳቦችን በጥሞና ማዳመጥና መመርመር ይገባል። ግልጽ ያልሆኑ ነገሮች ግልጽ እንዲሆኑ መጠየቅ አስፈላጊ ነው።ሀሳቡ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ከተገኘ የሃሳቡን አፍላቂ ሰው ስብእናና ክብር ሳይነኩ አማራጭ ሀሳብ ማቅረብ እንዲሁም የቀረበው ሀሳብ ጠቃሚ እንዳልሆነ በጨዋነት ማስረዳት ይቻላል።

ያሉትን ችግሮች ለማስረዳትና አዳዲስ መፍትሄዎችን ለመጠቆም ከቡድናዊ ህሳብ(ግሩፕ ቲንክ ) መላቀቅ ያስፈልጋል። ቡድንን ለመምሰል ባለስልጣንን ላለማስከፋት በሚል ሀሳብን ያለመግለጽ እና በጽናት አለመከራከር ሊወገድ ይችል የነበረውን ጥፋት ከማስወገድ ሊያግድ ይችላል። ለምሳሌ ቻሌንጀር (በህዋ ላይ የተቃጠለችው መንኩራኩር) መሬት ለቃ ከምሄዷ በፊት ችግር እንደነበረባት የጠቆሙ ኢንጂነሮች እንደነበሩና በግሩፕ ቲንክ ስለተሸነፉ ሊወገድ ይችል የነበረውን ጥፋት ማስቀረት አልቻሉም ነበር። በዲያስፖራ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መካከል ግሩፕ ቲንክ በቀላሉ የሚታይና በታወቁ መድረኮች ላይ የሚተገበር አዎንታ ነው። ነገር ግን ጥልቅ አስተሳሰብ በግለሰብ አእምሮ ውስጥ የሚፈጠር እንጂ በቡድን ውስጥ በአንድ ጊዜ በብዙዎች አእምሮ የሚፈጠር አይደለም። ለዚህም ነው የግለሰብ ህሳብን የመግለጽ መብት መከበር እጅጉን አስፈላጊ ነው የምንለው።

የለውጥ አስቸጋሪውና ከፍተኛው ደረጃ የማይፈልጉትን ማስወገድ ብቻ አይደለም። ይልቁኑም የሚፈልጉትን ነገር በተግባር መግለጽ ነው። ይህም ማለት ባንድ አገር ውስጥ ያሉ የዜጎችን አስተሳሰብ እና ባህል ማሳደግ ነው። የነበሩትን መንግስታት መጣል ብቻውን የተሻለ ስርአት እንደሚፈጥር የሚያረጋግጥ ዋስትና የለውም። ነገር ግን የአንድ አገር ዜጎች በግለሰብ ደረጃ የሰለጠኑ ያወቁና ከማንም ተጸእኖ ውጪ ሆነው እራሳቸውን የቻሉ የህሊና ፍርድ ሊሰጡ የሚችሉ ዜጋዎች በብዛት መኖር በጎ ለውጥ ማምጣትና የመጣውን ለውጥ ቀጣይነትና ዘለቄታዊነት እንዲኖረው ያደርጋል። ሰዎች ደግሞ እንዲማሩና እንዲሻሻሉ ለተሻሻሉ አስተሳሰቦች የተጋለጡ መሆን የኖርባቸዋል። ስለዚህ አሁንም በድጋሚ ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ አስፈላጊነቱ ይረጋገጣል። ገንቢ የሆነ ሀሳብ በአድማጮች ዘንድ ትክክለኛነቱን እንዲረዱ ረዘም ባለጊዜ ውስጥ በተደጋጋሚ እንዲነገሩ ያስፈልጋል። አንዳንዴም ሃሳቦችን በሙከራ ጣቢያዎች ሰርቶ ማሳየት ሊያስፈልግ ይችላል። የተሻሉ ሃሳቦች ተቀባይነት ሊዘገይ ይችላል እንጂ ብዙውን ጊዜ አይቀሬ ነው። እነዚህ የተሻሉ ሃሳቦች በመነጩበትና በታወቁበት ወቅት በሌላ ውድቀት ሊያስከትሉ በሚችሉ አስተሳሰቦች ሳይሸነፉ በፍጥነት ተግባራዊ መሆናቸው አላስፈላጊ የሆነ የጊዜ መዘግየትንና ኪሳራን ያስወግዳሉ። ይህን ሁኔታ ለመፍጠር ማሠብና መመራመር ይጠይቃል።

ትክክለኛ አስተሳሰቦች እንዲሁ በቀላሉ የሚገኙ አይደሉም። ፍላጎትን፣ ጥረትን፣ ተመክሮና እውቀትን እንዲሁም ምርምርን ይጠይቃሉ። የተለያዩ አማራጮችን ገምግሞ የላቀውን አማራጭ መምረጥ ቀላል ስራ አይደለም። ወደትክክለኛው ምርጫና ገንቢ ሃሳብ ለመድረስ ብዙ መሰናክሎችን ማለፍ ይጠይቃል። በእርግጥም ትክክለኛውን ሀሳብ ማፍለቅ ብዙ ማሰላሰልና ጊዜን ይፈልጋል። ነገር ግን ይህ ፈተና በራሱ አልበቃ ብሎ ከእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በዋዛ ያልተገኘውን እውቀት ለመግለጽ የአስቸጋሪና ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታዎች መፈጠር የሀሳቡን አፍላቂ ችግሮች በብዙ እጥፍ ያባዛዋል። የትክክለኛ ሃሳብ አፍላቂዎች ያላቸውን አስተሳሰብ በነጻነት ለመግለጽ ራሱን የቻለ ትግል ሲሆን የሀሳቡ ተሸካሚዎች ሀሳባችንን ዋጋ ከፍለን መግለጽ ይኖርብናል ብለው እንዲነሳሱ የሚያደርጋቸው ኢንሴንቲቭ አይኖራቸውም። ስለዚህ በቀላሉ ለመደመጥ ከሚደረገው ውድድር ራሳቸውን ያገላሉ። ጥረታቸው ለራሳቸው ጥቅም ሳይሆን ለመላ ህብረተሰቡ ጠቀሜታ ስለነበር በእነዚህ አስተሳሰቦች አለመንሸራሸር መላ ህብረተሰቡ ይጎዳል። ለለውጥና ለእድገት አመቺ በሆኑ ማህበረሰቦች ውስጥ የተሻለ ሃሳብ የሚያቀርቡ ስለሚደነቁና ስለሚሸለሙ የተሻለ ሀሳብ ሲያገኙ ያለምንም ማቅማማት ወደ ህብረተሰቡ እንዲሰራጩ እንዲያደርጉ ይደፋፈራሉ። ሰዎች በጎ ነገር እንዲያስቡና በጎ ነገር እንዲሰሩ ማነሳሳት ትልቅ የህብረተሰብ አገልግሎት ነው። በአንጻሩ ሰዎች ሀሳባቸውን እንዳይገልጹ የራስ አፍላቂነትና አነሳሽነት ስሜታቸው እንዲቀዘቅዝ ማድረግ አንድን ህብረተሰብ ባለበት እንዲደቅቅ ወይም ወደኋላ እንዲመለስ ያደርጋል። ግለሰቦች አስተሳሰብ ሲያፈልቁ እና በሚመለከትው ፈሰስ በኩል ሲያቀርቡ ሀሳባቸው ትክክል ቢሆንም ባይሆንም ላጠፉት ጊዜና ልፋት ሊመሰገኑ ይገባቸዋል።

ሰዎች ትላንት ያደረጉትን ዛሬ የሚደግሙት ከሆነ ነገም እንደዛሬ ዛሬም እንደትላንት ይሆንና መሻሻል አይኖርም ።የሰዎች አስተሳሰብና ስነምግባር ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻል ይኖርበታል። እውቀትንና ስነምግባርን ለማሻሻል ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ ባህል ማደግ አለበት። በዚህ ሀሳብ ምልልስ ውስጥ ሁሉም የህብረተሰብ አባላቶች ተካፋይ መሆን ይኖርባቸዋል። ባንድ ህብረተሰብ ውስጥ ጥቂቶች ብቻ አዋቂና መሪ ሆነው ብዙሀኑ መሪዎች በሚሰጡት መመሪያ ብቻ መንቀሳቀስ እየተተወና ታሪክ እየሆነ የመጣ አካሄድ ነው። ሁሉም ሰው ባለበትና በደረሰበት እውቀትን እየገበየ ተመክሮውን እያዳበረ ድርሻው የሆነውን የራሱን ሀላፊነት መወጣት አለበት። በአንድ አካባቢ የተገኘው ጠቃሚ እውቀት ወደሌሎች ቦታዎች እንዲዛመትና በአዳዲስ ቦታዎች እንዲለመድ ጥረት መደረግ አለበት።

ህገራችንንና ማህበረሰባችን በተመለከተ ያሉ የተለያዩ አስተሳሰቦች ብይፋ ይነገሩ። ትክክለኛውን አስተሳሰብ አዳማጭ ይምረጥ። በመከባበር የማይጥሙንን ሃሳቦች ሰምተን የራሳችን አስተሳሰብ እንሰንዝር። እስከ በሁላችን ዘንድ ያለው አስተሳሰብ ይነገር በይፋ።